የሰ/መ/ቁ. 58920

የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች:** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አለምነው አበበ አካሌ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ህብረት ኢንሹራንስ አ/ማ - ቃልኪዳን ንጉሴ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት መነሻ በማድረግ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ በወቅቱ ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ አመልካችን የከሰሰው የመድን ዋስትና በገባለት የደንበኛው መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ያወጣውን ወጪ እንዲተካለት ነው፡፡ አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የሥረ ነገር ክርክር አቅርቦአል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎአል በዚህ መሠረትም አመልካች በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል የወጣውን ወጪ ብር 5,500 ከእነ ሕጋዊ ወለዱ ጋር እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 26 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በሥር ፍ/ቤቶች ውድቅ የተደረገው በሕጉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ክርክሩ ሊነሣ የቻለው አመልካች በተጠሪ የመድን ዋስትና የተገባለትን መኪና በመግጨት ጉዳት አድርሶአል በመባሉ ነው፡፡ ገጭቶ ጉዳት ያደረሰው መኪና የአመልካች ንብረት ከመሆኑም በላይ ሲሽከረከር የነበረውም በራሱ ማለትም በአመልካቹ እንደሆነ አላከራከረም፡፡ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች የይርጋ መቃወሚያ ያነሣው በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2143/1/ የተቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ክሱን የሰማው

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃሚያው ሣይቀበል የቀረው ለይርጋው መቃወሚያ አወሳሰን ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በንዑስ ቁ./1/የተመለከተው ሣይሆን፣ በንኡስ ቁ. /2/ ያለው ነው በማለት ነው፡፡ ጊዜው ከዚህ ድንጋጌ አንፃር እየታየ ሲሰላም የክስ ማቅረቢያ ጊዜው አልፎአል ሊባል አይችልም እሚል መደምደሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ደርሶአል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው አቤቱታ የይርጋ መቃወሚያውን በሚመለከት ያነሣው ዋነኛ የመከራከሪያ ነጥብ በወንጀል ተከስሼ አልተቀጣሁም፡፡ ስለዚህም በንኡስ ቁ. /2/ የተመለከተው ድንጋጌ ለጉዳዩ አወሳሰን ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡

በተጠሪ ደንበኛ መኪና ላይ ጉዳት ሊደርስ የቻለው በአመልካች ጥፋት አይደለም የሚል በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ይልቁንም ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ጥፋት ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሶአል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ነው ከተባለ ደግሞ ድርጊቱ በወንጀልም የሚያስከስስ /የሚያስቀጣ/ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ድርጊቱ /ጉዳቱ/ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የይርጋ ዘመኑ ርዝመት በወንጀል ሕጉ በተደነገገው መሠረት እንደሚሆን ከላይ በተመለከተው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2143/2/ ተደንግጎአል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለው ደግሞ ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑ ከሚታይ በቀር የድርጊቱ ፈፃሚ ተከሶ መቀጣት እግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም በወንጀል አልተከሰስኩም ወይም አልተቀጣሁም በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት ያለው አይደለም በመጨረሻም የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረጋቸው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 158634 ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 94803 ሐምሌ 13 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች በዚህ ሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡን ተዘግቶአል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ